# ኢሳት - የወያኔ እግር እሳት!!!

(የወንዶሰን ከብሩ)

ለሁለት አስርተ ዓመታት በመሰሪነትና አገር አጥፊ ዓላማን በማራመድ ወደር ያልተገኘለት ወያኔ በዚሁ ተግባሩ 'እየተሳካለት' ያለና ማፊያን ያስናቀ ቡድን ለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም። በተለይም ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ፍጹም በሆነ አምባገነናዊነትና ጭካኔ የኢትዮጵያን ህዝብ በተለያዩ 'የረቀቁ' ስልቶች፡ እንዲሁም በጉልበትና በጠመንጃ አፈሙዝ እየገዛ ያለበትና በዚህም ሂደት ለመቀጠል በ'ቆራጥነት' ወስኖ እየተጓዘ ለመሆኑ መረጃ ማቅረብ አስፈላጊ አይሆንም። በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን ፍጹም በሚባል መልኩ የጠላበት፡ በአገዛዙም እጅግ የተንገሸገሸበትና ወያኔን ከትከሻዉ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሽቀንጥሮ ለመጣል የሁኔታዎችን አመችነት በናፍቆት እየጠበቀ የሚገኝበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

የወያኔ ረቂቅ የጥፋት ስልቶች በርካታ ናቸዉ። በአገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሃገራት የምገኝ ኢትዮጵያዊያን ቁጣችን ሲገነፍል ይህን የህዝብ ቁጣ ለማቀዝቀዝ ብሎም ማፈን እንዲያስችለዉ ሲጠቀምባቸው ከቆዩ ስልታዊ ዘመቻዎች አንዱ 'የቤት ስራ" በመስጠት ኢትዮጵያዊያኑ ትኩረታቸውን ወደዚሁ 'የቤት ስራ' እንዲያዞሩ ማድረግ ነበር። ታዲያ ኢትዮጵያዊያኑ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በዋናው ችግር ላይ ትኩረት በመስጠት ፋንታ ወያኔ እየሰጠን ባለው የቤት ስራ ላይ ብዙ ጊዜና ጉልበትን ሲያጠፉ ይታያሉ።

አሁን ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የቤት ስራን መስጠት የኛ፤ የሰጠነውን የቤት ስራ መስራት ደግሞ የወያኔ ተራ የሆነበት ክስተት ተፈጥሯል። ነጻው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጪት ያስከተለው ፈታኝ የሚዲያ ጦርነት። ወያኔ በዚህ ምክንያት የሚይዝና የሚጨብጠውን በማጣቱ ራስ ምታት የሆነበትን ኢሳትን ለማጥፋት ትግል ጀምሯል። ድሮ ድሮ ወያኔን የምናዉቀዉ (በተለይም ደርግን ለመጣል ባደረገዉ ትግል) የተለያዩ የዉጊያ ዘመቻዎችን በርካታ ስያሜ በመስጠቱ ነዉ። ዘመቻ አግአዚ፡ ዘመቻ ዋለልኝ፡ ዘመቻ ቴዎድሮስ፡ ዘመቻ ጸሃይ ግባት፡ ወዘተ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸዉ። አሁን ደግሞ እንደ እሳት እየለበለበው ያለውን ኢሳትን ለማጥፋት 'ዘመቻ እሳትን" ጀምሯል።

ይህ በቅርብ ጊዜ ስርጪቱን የጀመረው ነጻውና አዲሱ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ባለፈው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስርጭቱን በስኬት መጀመሩ የታወቀ ሲሆን የድርጅቱን መመስረትና እያስተላለፈው ያለውንም ፕሮግራሞች አስመልክቶ እጅግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ደስታቸውን እየገለጹ ይገኛሉ። ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየመጡ ያሉት አስተያየቶችም፣ በዚህ ድርጅት ትከሻ ለይ የብዙዎች ተስፋ ካሁኑ መጫኑን ከማሳየታቸውም በላይ በርካቶች፥ ኢሳት ወያኔ በኢትዮጵያ ያለውን የሚድያ ሞኖፖሊ ከመስበር አኳያ ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋል የሚል ተስፋ ጥለውበታል። በኢትዮጵያ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ እና መረጃን የማግኘት መብት ተከብሮ ለማየት የምንጓጓውና የምንታገለው ሁሉ በኢሳት መወለድ እሰየው ብለናል።

ይሁን እንጂ ነጻ የሆነ መረጃ ለህዝብ እንዳይደርስ እንቅልፋን አጥቶ እየሰራ ያለው የወያኔው አገዛዝ ይህን ወጣት የሆነና ነጻ የሆነ መረጃንም ለህዝብ በማድረሱ ብቻ ከበርካታ ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ ድጋፍ እየጎረፈለት ያለን ድርጂት ለማጥፋትና የኢትዮጵያ ህዝብም እውነተኛ የሆነ ነጻ መረጃ እንዳያገኝ ለማድረግ

እስካሁን ድረስ ለሶስት ጊዚያቶች ስርጪቱን ማፈኑ በተለያዩ የዜና መረጃ ምንጮች በስፋት ተዘግቧል። ለዚህም አፈና ተግባር በሚሊየኖች የሚገመት ገንዘብ እያባከነ መሆኑንም መረጃወች ያሳያሉ። ወያኔ በአገራችን ተከታታይ አምባገነናዊ አገዛዞች ሙሉ ቁጥጥር ስር ሆኖ አድሎ የሞላበት ስራ ሲሰራ የቆየውን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አሁንም ለራሱ የሃሰት ምስክር ሆኖ እንዲያገለግለው እያደረገና የኢትዮጵያ ህዝብም ከዚህ ቴሌቪዥን ውጪ ሌላ እንዳያይ እየፈረደበት ይገኛል።

የወያኔው አገዛዝ የእግር እሳት የሆነበትን ኢሳት ለማጥፋት እንቅልፍ አጥቶ እየሰራ ያለ ቢሆንም በአንጻሩ ኢሳትን የመሰረቱ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች የወያኔን ተደጋጋሚ አፈና በመቋቋምና አማራጮችንም በመፈለግ የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ላይ ያሉ ከመሆናቸውም በላይ ወያኔ ኢሳትን ለማፈን ጊዜና ጉልበቱን ከሚያጠፋው በላይ እነሱም ለዚህ የቴሌቪዥን ስርጪት ስኬታማነት ጠንክረው እንደሚሰሩ በተደጋጋሚ ገልጸዋል። ወያኔ እንደከዚህ ቀደሙ ለኢትዮጵያዊያን የቤት ስራ እየሰጠ የመጫወቻ ጊዜው እያከተመ ይመስላል። ወያኔ ከኢሳት እየተሰጠው ያለውን የቤት ስራ በመስራት ተጠምዷልና።

እውነተኛ ኢትዮጵያዊያን እንደ ኢሳት ያሉ አማራጭ ሚድያዎችን ለማቋቋም እና ለመደገፍ የምናደርገው ጥረት የተቀደሰ ተግባር ነውና በርተተን ልንቀጥል ይገባናል። ያንም ስናደርግ ግን ወያኔ ባንጻሩ በገዛ ንብረቶቻችን ላይ እየፈነጨ እንደሚገኝም አንርሳ! እነዚህ ጠላቶቻችን እንዲሆኑ የተደረጉ እንደ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያሉ ድርጅቶች የኛ ንብረቶች ናቸውና የወያኔ ናቸው በሚል አንዘንጋቸው። እነዚህ ተቋማት ከወያኔ ቁጥጥር ስር ነፃ ወጥተው ወደ ህጋዊ ባለቤታቸው፤ ወደ ኢትዮጵያ ህዝብ ሊመለሱ እና በገለልተኛነት ህዝባቸውን እንዲያገለግሉ ሊደረጉ ይገባልና።